# መስቀል፡ኃይላችን፡ነው።

የነገረ፡መስቀሉን፡መነሻ፤

የታሪኩን፡መዳረሻ፤

መርምራ፡ለማወቅ፡ብትሻ፤

እመ፡ቆስጠንጢኖስ፡ንግስት፡እሌኒ፤

ተደብቋት፡መቼ፡ቀረ፤

ምስጢር፡ሆኖ፡እንደተቀበረ።

በባዕድ፡ሃገር፡በኢየሩሳሌም፤

ሐይማኖቷን፡ጠበቃ፤

ለዕውነት፡ተነስታ፡ፀንታ፡ታጥቃ፤

ተራ፡ሰው፡መስላ፡ራሷን፡ንቃ፤

መስቀሉን፡አስቀድማ፤

ስታስፈልግ፡በገጠር፡በከተማ፤

ኪራኮስ፡እስራኤላዊው፤

በአምላክ፡ቃል፡እያፅናናት፤

የመስቀሉን፡ቦታ፡እየመራት፤

ደመራውን፡ደምራ፤
የዕጣኑ፡ጢስ፡ምልክት፡ሆኖ፤
መስቀሉ፡ተገኘ፡ተቆፍሮ፤
ምቀኞችን፡አሳፍሮ።
ድውያንን፡እየፈወሰ፤
አንካሶችን፡እያረታ፤
ጎባጣዎችን፡እያቀና፤
ለምፃሞችን፡እያነፃ፤
ዕውራንን፡እያበራ፤
ሙታንን፤እያስነሳ፤
ዜናው፡ተሰማ፡በዓለም፡ዙሪያ።
ጥበበኞች፡ነን፡ባዮቹ፤
የአይሁድ፡ካህናት፡ግብዞቹ፤
መጎብኘታቸውን፡ያላወቁ፤
ሰላማቸውን፡የናቁ፤
መዳኛቸውን፡የረሱ፤

በስራቸው፡የረከሱ፤
መስቀሉን፡ቢቀብሩትም፤
አልቻሉም፡ሊሰውሩት፤
ከእሌኒ፡ንግስት፡ሊሸሽጉት፤
ዝናውን፡ከቁስጥንጥንያ፤
ከዚያም፡አልፎ፡በኢትዮጵያ፤
እየተባለ፡ሃሌ፡ሉያ።
እስኪ፡እኛም፡ይመርብን፤
የመስቀሉ፡ቃል፡እንዲያድርብን፤
በአዲስ፡ምስጋና፡በዝማሬ፤
ደመራውን፡እንደምራ፤
ተሰብስበን፡በመስቀሉ፡ዙሪያ፤
መስቀል፡ኃይላችን፡ነው፤
መስቀል፡ፅንአችን፡ነው፤
መስቀል፡ቤዛችን፡ነው፤
መስቀል፡የነፍሳችን፡መዳኛ፡ነው፤

እየተባለ፡ያስተጋባ፤
እየተበተነ፡የአደይ፡አበባ፤
መስከረም፡ጠባ፡ኢዮሃ፡አበባ፤
መስቀል፡ጠባ፡ኢዮሃ፡አበባ።

ከኃይለመስቀል፡ተስፋዬ
ለንደን